***የስብሰባው ዓይነት፡ የመስራች ጉባኤ የመዝጊያ ንግግር***
***ቀን፡ መጋቢት 15 2011***
***ቦታ፡ ካፒታል ሆቴል***

ክቡራን የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ አባላት

የተከራችሁ የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት

ውድ የስራ አስፈጻሚና የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን አባላት

**ክቡራትና ክቡራን**

ከሁሉ አስቀድሜ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲን ለመመስረት ላለፉት በርካታ ወራት በአዲስ አበባ እና በሁሉም ክልሎች የተለያዩ ስራዎችና ኃላፊነቶች ወስዳችሁ ሌት ተቀን ስትሰሩ ቆይታችሁ በዛሬው እለት የፓርቲያችንን ምስረታ እውን ማድረግ በመቻላችሁ የተሰማኝን ታላቅ ደስታ በራሴ እና በመላው የፓርቲያችን አባላት ስም መግለጽ እወዳለሁ፡፡

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሀገራችን በበርካታ ውስብስብ ችግሮች በተጠመደችበት፣ አስታራቂ እና አሰባሳቢ የጠፉ በሚመስልበት፣ ከመሰባሰብ ይልቅ መለያየት በበረከተበት፣ ከአንድነት ይልቅ ልዩነቶች በተስፋፋበት የታሪክ አጋጣሚ አዲስ ራእይ፣ አዲስ ጉልበት፣ አዲስ ተዋናዮችን ይዞ ሀገራችንን እና ህዝባችንን ለመታደግ የተወለደ ፓርቲ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የዛሬዋ ቀን በኢትዮጵያ የፖለቲካ ህይወት ውስጥ ታሪካዊ ናት፡፡ እንደ አንድ የፓርቲው አባልና መስራች ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በርካታ አዳዲስ ነገሮችን ለሀገራችን ያበረክታል ብዮ ሙሉ እምነት አለኝ፡፡

- ድህነት፣ የፍትህ፣ የሰላምና መረጋጋት እጦት፣ መድሎ፣ የመረረራቸው፣ የህይወት ሸክም ጎናቸውን ያጎበጠው፣ እልፍ ወገኖቻችን በተስፋ ይጠብቁናል፡፡
- ብሄር፣ ሀይማኖት፣ ቋንቋ፣ ክልል ሳይለያያቸው በአንድነት፣ በወንድማማችነትና በእህትማማችነት፣ መኖርን አጥብቀው የሚሹ ግን በአንዳንድ የተሳሳቱ አመለካከቶች የተለያዩ፣ ወገኖቻችን በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች እጃቸውን ዘርግተው ይጠብቁናል፣
- ህጻናት፣ አረጋውያን፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች ከሚገኙበት ከባድ የህይወት ፈተና አላቆ የተከበረ ህይወት እንዲኖሩ ምርኩዝ የሚሆናቸው ወገን በተስፋ በጸሎት ይጠብቁናል፡፡
- ለታመሙ ፈውስ፣ ተምረው ራሳቸውንና ሀገራችውን ለመቀየር ለሚሹ ነገር ግን ከባድ የድህነት ቀንበር ህልማቸውን እውን ማድረግ እንዳይችሉ ላገዳቸው የትምህርት እና የእውቀት ችቦን እንድናቀጣጥልላቸው በጉጉት ይጠብቁናል፣
- ብዙ መስራትና አዳዲስ ነገሮችን መፍጠር እየቻሉ አስታዋሽ አጥተው ተስፋ ለጨለመባቸው በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ወጣቶቻችን የስራ እድል እንድንፈጥርላቸው ሚሊዮኖች ይጠብቁናል፣
- ነጻነትና እኩልነት እንደ ውሀ የጠማቸው፣ በሀገር እና በህዝብ ፍቅር ልባቸው የተሞላ ሰርተው የሚያሰሩ ቅን መሪዎችን የሚጠብቁ ሰፊ ህዝብ በጉጉትና በተስፋ ይጠብቀናል

***የተወደዳችሁ የፓርቲያችን አባላትና አመራሮች፣***

ከፊታችን ትልቅ ኃላፊነትና አያሌ ውጣ ውረዶች ይጠብቁናል፡፡ ህዝባችን ለዘመናት ከተጫኑበት ዘርፈ ብዙ ችግሮች ጋር የሞት ሽረት ትግል ሲያካሂድ፣ በየግዜው አዳዲስ ችግሮች ብቅ እያሉ ሸክሙን አክብደውበታል፡፡ ህዝባችን የሚፈልገውን ሰላምና ልማት እውን ለማድረግ ሌት ከቀን መስራት ይጠበቅብናል፡፡ ፓርቲያችን አዲስ እንደመሆኑ ዛሬ የመረጥናቸው የፓርቲችን መሪዎች እና መላው አባላት በሚቀጥለው አንድ አመት ከፍተኛ ኃላፊነት እና ዘርፈ ብዙ ስራዎችን መስራ

ግድ ይለናል፡፡ መስራት ከሚገባን ስራዎች መካከል የፓርቲውን ሁለንተናዊ አቅም መገንባትና ፓርቲውን ማስተዋወቅ ትኩረት የሚሹ ስራዎቸ ናቸው፡፡

ከአቅም ግንባታ ጋር በተያያዘ የፓርቲያችንን መዋቅር በክልል፣በዞን፣ በወረዳና ቀበሌ መዘርጋት፣ በሰው ኃይል፣ በአደረጃጀት፣ በፋይናንስና በቴክኖሎጂ ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ በተለያዩ የፖለቲካ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የህግ ጉዳዮች ሰፊ የአባላት ስልጠናና ኢንዶክትሪኔሽን ስራ መስራት ይጠበቅብናል፡፡

ፓርቲውን ለተለያዩ የባለድርሻ አካላት ጋር ለማስተዋወቅ፣ ከፌዴራልና ከክልል መንግስታ አካላት ጋር ውይይት በማድረግ የፓርቲውን ራእይና ዓላማዎች ግልጽ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሀገራችንን ካላችበት የረዠም ግዜ እና አፋጣኝ ወቅታዊ ችግሮች የምትላቀቅበትን የመፍትሄ ሃሳቦችን ማቅረብ ከዋና ዋና ስራዎቻችን መካከል ሊሆን ይገባል፡፡

የተከበራችሁ የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ዓላማችንን ለመሳካት በምንቀሳቀስበት ጊዜ እና ቦታ የፓርቲያችን መርሆችን ሁሌም ልናስታውስ ገባል፡፡

- በመግባባት ላይ የተመሰረተና ከፍጥጫ የራቀ የፖለቲካ ትግል፡
- ሚዛናዊነት እና አሳታፊነት፡
- ተፈጥሯዊ ለውጥ፡
- አብሮ ማሸነፍ፡
- ህዝብን ማገልገል፡
- እውነተኛነት እና ታማኝነት የሚሉት እሴቶቻችን የእንቅስቃሴአችን ማእቀፍ አድርገን መንቀሳቀስ ይኖርብናል፡፡

**በመግባባት ላይ የተመሰረተና ከፍጥጫ የራቀ የፖለቲካ ትግል መርሀችን** ከማናቸውም የፖለቲካ ኃይል ወይም ድርጅት ጋር በኃላፊነትና በሀገር ፍቅር ስሜት እንድንሰራ ያስገድደናል፡፡ ሀገራችንን እና ህዝባችንን በሚጠቅሙ ጉዳዮች ዙሪያ ማንኛውም አይነት የፖለቲካ ርእዮተ-ዓለም ወይም ፕሮግራም ካለው የፖለቲካ ድርጅት ጋር በትብብር እንሰራለን፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሌሎች የፖለቲካ፣ የሲቪክና ማህበረሰብ እና የግል ዘረፍ ውስጥ ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር በህብረት እና በቅንጅት እንንቀሳቀሳለን፡፡

**የሚዛናዊነትና አሳታፊነት መርሀችን** የህዝባችንን የብሄር፣ የቋንቋ፣ የሀይማኖት፣ የባህል ብዝሀነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በፖሊሲና ፕሮግራም፣ በቋንቋ አጠቃቀም፣ በፖለቲካዊ አቋም፣ ወዘተ ሚዛናዊ አካሄድ እንድንከተል ግድ ይለናል፡፡ የግለሰብ ወይም የቡድን መብትና ስሜትን ሊጎዱ ከሚችሉ ድርጊቶች እንቆጠባለን፡፡ ከዚህም በላይ በሀገር አቀፍ፣ በክልል፣ በዞን በወረዳና ቀበሌ በምንዘረጋቸው መዋቅሮች ሁሉንም የሀገራችንን ህዝቦች ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ለማቀፍና ለማካተት በርትተን እንሰራለን፡፡

**የተፈጥሯዊ ለውጥ መርሀችን** በሀገራችን ያለው የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በረዥም ዘመናት ሲጠራቀሙና ሲደራረቡ የቆዩ በመሆናቸው በአንድ ጀንበር ሊቀረፉ እንደማችሉ ይነግረናል፡፡ በመሆኑም በትእግስታና ኢትዮጵያዊ ጨዋነት ጠንክረን መስራት ይጠበቅብናል፡፡ በአንድ ጀንበር ውጤት መጠበቅ እና የተስፋ መቁረጥ ስሜት በውስጣችን ከቶም ሊኖር አይገባም፡፡

**ለእኛ** እውነተኛ ማሸነፍ የሀገር እና የህዝብ ማሸነፍ ነው፡፡ በማኛውም ግዜና ሁኔታ ከድርጅታዊ ድል እና ስኬት ይልቅ የሀገርንና የህዝባችንን ድልና ስኬት ልናስቀድም ይገባል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የፓርቲያችን ውጤታማነትና ስኬት

በሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ውድቀት ላይ ሳይሆን አብሮ በማደግ እውነተኛ የአጋርነት ስሜት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ አስተሳሰብ **የአብሮ ማሸነፍ መርሀችን መገለቻ ነው፡፡**

የአንድ የፖለቲካ እንቅስቃሴና የፖለቲካ ስልጣን ትልቁና የመጨረሻ ግብ ሀገርንና ህዝብን ማገልገል ነው፡፡ ህዝብን እንዲያስተዳድሩ በህዝብ የሚወከሉ የፓርቲና የመንግስት ኃላፊዎች ከድሀው ህዝባችን ላብ ተቀንሶ ከሚሰበሰብ ግብር የሚከፈላቸው ናቸው፡፡በመሆኑም በየትኛውም የኃላፊነት ደረጃ የሚገኙ የድርጅታችን አባላት የህዝብ አገልጋይ ሆነው ይሰራሉ፡፡ ይህ ህዝብን የማገልገል መርሀችን መገለጫ ነው፡፡

**እውነተኛነት እና ታማኝነት የፓርታያችን አባላትና አመራር በመላው ኢትዮጵያውያን ዘንድ ልንታወቅበት የሚገባ መለያ ሊሆን ይገባል፡፡** የሀገራችን ህዝቦች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ለእውነተኛነት፣ ቅንነት እና ታማኝነት ላቅ ያለ ግምት እንደምንሰጥ ሁሉ የድርጅታችን መደበኛ አባልም ሆነ አመራር ሀገራችንና ህዝባችንን በእውነተኛነት፣ በታማኝነት እና በፍቅር ልናገለግል ይገባል፡፡

**የተወደዳችሁ አባላት**

ለአንድ የፖለቲካ ድርጅት ውጤታማነት መሰረት ከሚሆኑ ጉዳዮች አንዱ የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲ ነው፡፡ ለዴሞክራሲ የሚታገል አንድ ድርጅት በቅድሚያ በውስጡ ዴሞክራሲያዊ አሰራሮችንና መርሆችን ለከተል ይገባል፡፡ በመሆኑም በፓርቲያችን በየትኛውም የኃላፊነት ደረጃ የምንገኝ አባላት የፓርቲውን ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ ማደረግና የተጣለብንን ግልጽነት እና ተጠያቂነት በተመላበት ሁኔታ

**ውድ የነእፓ ቤተሰቦች**

ፓርቲያችን በምስረታ ላይ በነበረበት ወቅት ካካሄዳቸው ስራዎች አንዱ ከመንግስት እና ከአቻ ፓርቲዎች ጋር ጠንካራ የስራ ግንኙነት መመስረት ነበር፡፡ በዚህም ከመንግስት በተለይም ከብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ጋር መልካም የስራ ግንኙነት መመስረት የተቻለ ሲሆን በተለይም በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት እንዲሁም ፓርቲዎች በተናጠል የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች የሚገዛ የአሰራር ሰነድ በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ አድርገናል፡፡ በሰነዱ ላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሰፊ ውይይት ካደረጉበት በኃላ የፊርማ ስነስርአቱ ላይ በመገኘት ሰነዱን አጽድቀናል፡፡ የቃል ኪዳን ሰነዱ በሀገራችን ጠንካራ እና ዘላቂ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት፣ ሀገራችን የተጀመረውን የለውጥ እንቅስቃሴ ለማስቀጠልና ሀገራችን ወደተሻለ ዴሞክራሲ እንድትሸጋገር ለማድረግ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ኃላፊነት በተሞላበት አካሄድ የሀገርን ብሄራዊ ደህንነት እና የዜጎችን ነጻነትና መሰረታዊ መብት ማስጠበቅ በሚያስችል ደረጃ እንዲሳተፉ ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የቃል ኪዳን ሰነዱ አንድ አካል በመሆኑ ለሰነዱ ዓላማዎች መሳካት ሙሉ ድጋፍ ማድረግ ይኖርብናል፡፡የገባነው ቃል ኪዳን በተለይ እንደኛ ላሉ አዲስ በመቋቋም ላይ ለሚገኙ ፓርቲዎች ከሌሎች ሀገር አቀፍና የክልል የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በጋራ እና በመተባባር ለመስራት ምቹ አጋጣሚን የሚፈጥር ሲሆን በተለይም የተቋቋመው የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ለዚህ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ በምናደርጋቸው የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች በሰነዱ የተካተቱ ዝርዝር አንቀጾች እና መንፈስ በመረዳት ለተግባራዊነቱ የአቅማችንን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

**ውድ የነእፓ አባላት**

**የተከበራችሁ የነእፓ አመራሮች**

ሁላችሁም እንደምታውቁት ብሄራዊ ምርጫ ከፊታችን እየመጣ ነው፡፡ ምርጫው ሀገራችን የጀመረችውን የለውጥ እና የዴሞክራሲ ጉዞ በአስተማማኝ መሰረት ላይ ለማስቀመጥ ያለው ድርሻ ከፍተኛ ሲሆን ምርጫው የተሳካ እንዲሆንና ፓርቲያችንም በምርጫው ውጤታማ ይሆን ዘንድ ስራ የምንጀምረው ዛሬ ነው፡፡ ከምርጫ ጋር ተያይዞ የሚሰሩ በርካታ ስራዎች ያሉ ሲሆን የምርጫ ማኔፌስቶ ማዘጋጀት፣ አባላቶቻችንን በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ስልጠናዎች መስጠት፣ ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በጋር የምንሰራበትን የትብብር መድረኮችን መፍጠር ከብዙ በጥቂቱ ናቸው፡፡ የምርጫው ውጤት በመራጩ ህዝብ፣ በተፎካካሪ ፓርቲዎችና፣ በታዛቢዎች ተቀባይነት ያለው እነዲሆን እና አላስፈላጊ ድህረ ምርጫ ችግሮች እንዳከሰቱ አቅማችን የሚፈቅደውን ያህል እንሰራለን፡፡

በመጨረሻም ለፓርቲያችን መመስረትና ለጉባኤው መሳካት በተለያየ መንገድ አስተዋጾ ላደረጋችሁ አባላት፣ የጉባኤ ዝግጅት ሂደት የተሳካ እንዲሆን አስተዋጾ ላደረጉልን የመንግስት አካላት በተለይም ለብሄራዊ ምርጫ ቦርድ አመራርና ሰራተኞች በመላው የፓርቲያችን አባላት ስም ከፍ ያለ ምስጋናችንን ፡፡

መጪው ዘመን በሀገራችን ነጻነትና እኩልነት፣ ሰላምና መረጋጋት፣ እድገትና ብልጽግና፣ አንድነትና ወንድማማችነት፣ ዴሞክራሲና ፍትህ እንዲሆም የህግ የበላይነትና  የሰፈነበት እንዲሆን እየተመኘሁ፣ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ በነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የትግል አርማ ስር ሆነን በይፋ ወደ ስራ የገባን መሆናችንን አበስራለሁ

አመሰግናለሁ፡፡